# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

የመፅሔት አዘጋጅ ቦርድ፥
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር፡ 3
ጥር 1966

## የትግላችን ትርጉም::

# የመዋሀዱ ዘመቻ

ባለፈው 'ትግላችን' ቁጥር በዚሁ ዓምድ ስር በጓዱ መገስ የቀረበው ጽሁፍ ስለ ተራማጅ ተማሪዎች ተግባር በሚገባ አብራርቷል:: ይህ ጓዱ በተማሪ ንቅናቄ ውስጥ የምንገኝ ተራማጆች ዛሬ በዴሞክራሲ ጥያቄዎች እየተነሳሳ በሚደረገው ትግል በሰፊው መሳተፍና ለመጭው ትግል ደግሞ ራሳችንን ማነጽ እንደሚገባን ያሳስባል:: በኔ አስተያየት ይህ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ተራማጆች ጊዜያዊና ተቀዳሚ ተግባር ነው እላለሁ:: ከዚህም በመነሳት ዛሬ 'የትግላችን ትርጉም' ምን እንደሆነ በይበልጥ ለመረዳት የጓዱ መገስ ጽሁፍ በሁለት አቅጣጫዎች መስፋፋት አለበት::

አንደኛ የነዚህ 'ጥንዱ ተግባሮች' ይዘትና በዛሬው ወቅት የምንሰጣቸው ቀደም ተከተል መጣራት አለበት:: ሁለተኛ ደግሞ ይህ አቋም ከሌሎች አቋሞች የሚለይበት ነገር መታየት አለበት::

የነዚህ ጥንዱ ተግባሮች ይዘት ምንድን ነው:: በኔ አስተያየት በዛሬው ትግል መሳተፍ ሲባል፣ በፕሮፓጋንዳና በአጂቴሽን <u>በትንሹም በትልቁም</u> የሬዥሙ ወገን የሆኑ ኃይሎች ሁሉ በሚያነሷቸው ጥያቄዎች እየተነሱ ስርዐቱን ማጋለጥ፣ መታገልና ከያለበት ማዋከብ ነው:: በዚህ መልክ ከሰፊው ህዝብ ትግል <u>በግንባር ቀደምነት</u> የምንዋሃደው እስከዚህም እኛ በምንወስናቸው፣ እና ከአንጎላችን ወይም ደግሞ ከመጸሀፍቶቻችን በምናፈልቃቸው ጥያቄዎች አይደለም:: በዕለታዊ ኑሮው ህዝቡን በሚያስጨንቁትና ከመንግሥቱ ጋር በሚጋጭባቸው ነገሮች እየተመረኮዝን ነው:: የማህበራችን መሪ ቃል አንዱ ክፍል ከህዝቡ ተዋህዱ ካለ በኋላ ወዲያው አስከትሎ '<u>ከሱም ተማር</u>'

የሚለው ይህንኑ ለማመልከት ነው:: ከህዝቡ የምንዋሀደው ጥያቄዎቹን ከሱው ተምረንና እነሱን ይዘን አብረነው እንድንታገል ነው::

ግን እዚህ ላይ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ይህ መዋሀዳችን ሬቮሉሽናዊ ትርጉሙን እንዳይስት የጥንድ ተግባራችን ሌላው አካል መረሳት የለበትም:: የማህበራችን መሪ ቃል ከህዝቡ ተዋሀዱ ከሱም ተማር ካለ በኋላ አሁንም ወደያው በማከታተል "መልስህም አስተምረው" ይላል:: ህዝቡ ሲታገል አብረነው እንታገል ስንል በሱው ጥያቄዎች ብቻ ተውጠን እንቅር ማለታችን አይደለም:: ከህዝቡ ስንዋሀድ በግንባር ቀደምነት ነው እንጂ እንደሁ መደባለቅ አይደለም:: አብረነው ስለምንታገል፣ችግሩን ችግራችን ስላደረግነው የህዝቡን ተደማጭነትና ዕምነት እናገኛለን:: በዚህም በመመርኮዝ ስለ ዘላቂው ትግል ስለ ዕውነተኛ ወዳጆቹ፣ ስለ ዕውነተኛ ጠላቶቹ ስለ ጊዜው ትግል ታክቲክ፣ ስለ ዘላቂው ትግል ዓላማ እያስረዳን የትግሉን ደረጃ በየዕለቱ ከፍ ለማድረግ መጣር አለብን:: ከሱ ጋር ስለተዋሀድን የጥገና ለውጥ ደጋፊዎች እንደሚያደርጉት ዘላቂውን ትግል ፈጽሞ መርሳት አይገባም:: ግን ደግሞ አንዳንድ አጉል ተራማጆች ወይም ግራ ቀደሞች እንደሚሉት "ዋናው ዘላቂው ትግል ነው" በሚል አጉል ፈሊጥ በትንሽም በትልቅም ዛሬ ከህዝቡ ጉን መሰለፍን እንደ ጊዜ ማጥፋት ልንቆጥረው አይገባም::

እንግዲህ እነዚህ ጥንድ ተግባሮች እጅግ የተያያዙ መሆናቸው የሚታየው እዚህ ላይ ነው:: ተራማጆች ከህዝቡ መዋሀዳቸው ፍሬ እንዲሰጥ ከህዝቡ ተለይተው በአንድ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት መተሳሰር አለባቸው:: እንደዚሁም ደግሞ ከህዝቡ ተለይተው መደራጀታቸው ፍሬ እንዲሰጥ ከህዝቡ ተዋሀደው ትግሉን በግንባር ቀደምነት መምራት አለባቸው::



ተራማጅ ነኝ ብሎ ይህን ዕውነት የማይቀበል ያለ አይመስለኝም:: ከህዝቡ መዋሀድና በአንድ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት መተሳሰር በአንድ ሳንቲም ላይ እንዳሉ "ዘውድና አንበሳ" የአንድ ነገር /ማለት የሬቮሉሽናዊ ትግላችን/ ሁለት መልኮች ናቸው:: ነገር ግን በአንድ በተወሰነ ጊዜ በአንድ በተወሰነ አካባቢ ሁለቱንም በአንድ ኃይል ልንሰራባቸው አንችልም:: አንድ መኪና ቤንዚን መስጫም ፍሬን መያዣም አለው ብለን ሁለቱንም በአንዴ ረግጠን መያዝ አንችልም:: አለበለዚያ መኪናው አገልግሎት አይኖረውም:: እዚህም ላይ እንደዚሁ ነው:: እንደ ጊዜው፣ እንደ ትግሉ ሁኔታ እየታየ አንድ ጊዜ ለአንደ አንድ ጊዜ ለሌላው ተግባር ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል:: አለበለዚያ ትግላችን ወደፊት ሊገፋ አይችልም:: እንግዲህ እዚህ ላይ ጥያቄው ዛሬ በ1966 ዓም የኢት. ተራማጆች እነዚህን ጥንድ ተግባሮች እንደያዙ ለየትኛው ቅድሚያ ይስጡ አመዛኙ ጉልበታቸው ወደት ያድላ የሚለው ጥያቄ ነው:: ልዩነትም የሚነሳው እዚህ ላይ ነው::

በአንድ በኩል ለቴዎሪ ጥናት፣ጥቂቶችን ከህዝቡ ለይቶ ለማነጽ፣ ለማደራጀትና ለማሰናዳት ቅድሚያ የሚሰጡ አሉ:: ይህ አቋም ራሱ እኔ እንደታዘብኩት ሁለት አዝማሚያዎች አሉት:: አንደ ቸኩልነት የሚያጠቃው አጉል ተራማጅ /ግራ ቀደም/ አቋም ነው:: ሌላው ደግሞ ዲተኛና ተስፋ ቆራጭ አቋም ነው:: ቢሆንም ሁለቱንም አንድ የሚያደርጋቸው ነገር አለ:: እና ዛሬ ዋና ነው የምንለውን በትንሽም በትልቅም ከህዝቡ ጉን መሰለፍ ነው ብለን የምንተልመውን "የመዋሀድ ዘመቻ" በየምክንያቱ ቸላ ይሏሉ:: ይንቃሉ::

ቸኩሎና ግራ ቀደሙ አቋም ምን ይላል:: ዛሬ በኢት. ለሬቮሉሽናዊ አመጽ የተመቻቸ/ኢንዚሬክሺነሪ ሲቹዌሽን/ ሁኔታ አለ ብሎ ያምናል:: ሌላው ቀርቶ "ወደ ኋላ የቀሩ ገበሬዎች እንኳን መሳሪያ ይዘው ተነስተዋል" ስለዚህ ለዚህ

ትግል ሊነሱ ይችላሉ የሚል ዕምነት አለው:: እንግዲህ ለዚህ የሚያስፈልገው በተቻለ ፍጥነት የተገኙትን ቁራጮች አሰባስቦ አንድ አነስተኛ ድርጅት/ሚኒሙም አርጋናይዜሽን ይሉታል/ ማቋቋምና የህዝቡን የጠር ትግል መምራት ነው:: ስለዚህም ለዚህ ዓላማው ሲወጣ ሲወርድ፣ ያው ዋናውና 'የለየለት' መዋሀድ እስከመጣ ድረስ በዚች በትንሽ በትልቋ ከህዝብ ጉን እየተሰለፈ በፕሮፓጋንዳና በአጅቴሽን ህዝቡን ቀስ በቀስ ማነጻን እንደ 'ጊዜ ማጥፋት' ይቆጥረዋል:: 'ትግላችን' አድሃሪውን መንግሥት ለማጋለጥ፣ በየሸርኩቻው የምትደረገዋን የህዝብ ትግል ለማስተጋባት አቅሙ የሚፈቅድለትን መረጃዎች ሰበሰቦ ለአንባቢዎቹ ሲያቀርብ 'የመንደር ወሬ' አበዜ ብሎ ያማርራል:: እንደዚህም ይልና ሬቮልሽናዊ የሆነ ፖርቲ እንዴት እንደሚቋቋም፣ አባሎቹ በምን መራል ተመርተው መታገል እንዳለባቸው .... የሚገልጽ 'ሀንድ ቡክ ለን ሬቮሉሽን...' መጽሄት አውጥቶ ተራማጆች በቃል እንደያጠኑት ጋበዘ ያስራጫል::

ዓተኛው አቋም ምን ይላል:: እሱ ደግሞ የሚለው ዛሬ እና ተራማጆች የሃገሪቱን ሁኔታ በሚገባ ስለማናውቅ፣ በቂ ጥናት በላልተደረገ፣ ብዙ ነገሮች ስለሚጎድሉን፣ በዚህ ሁሉ የተነሳ ለህዝቡ ትክክለኛ የሆኑ የመቀስቀሻ መሪ ቃሎች /ስሎጋንስ/ 'ለመስጠት' ስለማንችል/ የህዝቡን የትግል መነሻዎች ከሱው ሳንዋሀድ ከቲዎሪና ከመጽሀፍ እናገኛቸው ይመስል/ ለሬቮልሽኑ የተጣራ የሥራ ትልም ለማውጣት ገና በደንብ ስላልተጠና፣ በሚገባ ለመዋሃድ ከፈለግን አስቀድመን ተደራጅተን የተቀናበረ ጥናት ማድረግ አለብን ይላል::

ከነዚህ ከሁለቱ አስተሳሰቦች ተለይቶ ማህበራችን በዕለታዊ ተግባሩም ሆነ በሚያወጣቸው መጽሄቶች ለመከተል የሚሞክረው ሬቮልሽናዊ መስመር አለ:: ከህዝብ መዋሀዱም ሆነ ተለይቶ መደራጀቱ የተሳሰሩ ጊዜያዊ ተግባሮች ቢሆኑም ዛሬ



ተራማጆች ተደራጅተው ተቀዳሚነት የሚሰጡት ተግባር በትንሹም በትልቁም ከህዝቡ ትግል እየተደባለቁ ትግሉን ከፍ ማድረግ ነው ይላል:: ይህ ቀዳሚያ ለምን::

በኔ አስተያየት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ:: አንደኛው ዛሬ የኢት. ተራማጆች የሚገኙበትን ደረጃ የሚመለከት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ የዛሬውን የሀገሪቱንና የህዝቡን ሁኔታ ይመለከታል::

በሁለተኛው ልጀምር:: ዛሬ በኢት. ጠቅላላ ሁኔታ ማንም ሊክደው የማይችለው አንዱ ሀቅ ቢኖር ህዝቡ የፖለቲካ ትግል ልምድ **ማጣ**ቱና የድርጅት ስልት አለማወቁ ነው:: ታዲያ ሬቮሉሽን ሲባል ደግሞ 'የግንባር ቀደሞች' ውር ውረ አይደለም:: ጠቅላላውን 'ለለውጥ ታጥቆ ለመቆት የተነሳ'/ሌኒን እንዳለው/ በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ ትግል ነው:: የጥቂት ወራትም ግርግር አይደለም:: ረዥምና አታካች ትግል ነው:: እንዲህ ስለሆነ ደግሞ ማንም የማያመልጠው መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን:: በሚልዮን የሚቆጠረው ህዝብ ገና አስፈላጊው የፖለቲካ ትግል ልምድ ከሌለው ተግባራችን ህዝቡ በዚህ ትግል ልምድ እንዲያገኝ ማገዝ ነው:: ህዝቡ የፖለቲካ ትግል ልምዱ የድርጅት ስልት ከሌለው፣ ሬቮሉሽን ደግሞ በተደራጀ አድሃሪዎች ፊት የተደራጀ ተጋዳይ ህዝብ ጉዳይ ከሆነ፣ ተቀዳሚ ተግባራችን ህዝቡ ቀስ በቀስ እንደደራጅ መንገዱን ማሳየት ነው:: እንግዲህ ሁኔታው እንዲህ ከሆነ ከዚህ ተጨባጭ የኢት. ሁኔታ በመፍለቅ ትከሻችን ላይ የሚወድቀው ሃላፊነት ከጸሀይ ደርቶ ሊታየን ይገባል:: እንደዚህም ሆኖ ሳለ አንዱ 'እንበለው' እያሉ ወደፊት በማፈትለክ፣ አንዱ ደግሞ 'እናጥና' እያሉ ከታሪክ ወደኋላ በማፈግፈግ ከጊዜው ተግባር፣ ከጊዜው አደራ፣ ከጊዜው ሃላፊነት ለማምለጥ መሞከር በኢት. ህዝብ ትግልና መከራ ማላገጥ ነው እላለሁ::

ይህንን የምልበት ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ዛሬ የኢት. ተራማጆች ራሳቸው የደረሱበትን ከፍተኛ ደረጃ በማየት ነው::

ሀገራችን በመከራዋ ሁሉ ተቆርቋሪና ተጋዳይ አገር ወዳዶች ተጓድሏባት አያውቅም:: ዛሬም በፊውዳሊዝም ጨለማና በኢምፔርያሊዝም ጭቆና ስር ወድቃ በምትዳክርበት ጊዜ ከመቸውም ይበልጥ ቆራጥ ተጋዳዮች ስታፈራ እናያለን:: እነዚህ የዘመኑ ተጋዳዮች ካደረባቸው የህዝብ ፍቅር በተጨማሪ በቲዎሪ ዕውቀታቸው የጊዜውን ዋና ጠላት ተንትነው ያወቁ ወጣቶች ናቸው:: የሬቮሉሽኑንም ጥርጊያ ጉዳና በግርዱፉ ተሠመው በሰው መሠረት ትግላቸውን የጀመሩ ናቸው:: በዚሁ በተተለመው ሬቮሉሽናዊ ጉዳና ላይ ጠላትን ሲተናነቁ ካሁኑ ብዙ ጓዶቻችን ለጋ ህይወታቸውን ለህዝባቸው ሰውተዋል:: ይህም ዛሬ በኢት. ለጊዜው ሬቮሉሽናዊ ተግባር በቂ ቆራጥነት ያላቸው፣ በቂ የቲዎሪ ዕውቀት የገበዩ ተራማጆች ለመኖራቸው በቂ ማስረጃ ነው:: እርግጥ ከህዝቡ ቁጥር ጋር ሲነጻጸሩ እፍኝ አይሞሉም:: እርግጥ ከሚጠበቀብንና ከሚጠብቀን ሬቮሉሽናዊ ተግባር ጋር ሲመዘኑ ገና ትንሽ ናቸው:: ነገር ግን የጊዜውን ተግባር በትክክል ከተረዱ፣ ይህን ተግባር ከስራ ላይ ለማዋል ከተሳሰሩ፣ ተሳሰረው ደግሞ በትንሹም በትልቁም ከህዝቡ ትግል ጋር ለመዋሀድ ከቆረጡ፣ የተራማጆች ትንሽ የላቸውም:: በሌላ በኩል ደግሞ ተቀዳሚውን ተግባር ስተው ባልሆነ አቅጣጫ ቢባክኑ፣ መ ተሳሰራቸውን ትተው በየፊናቸው ቢፍጨረጨሩ፣በትንሽ በትልቁ ከህዝቡ መዋሀድን እንደፍር በለው ወይም ንቀው በሆነ ባልሆነው ራሳቸውን “በግንባር ቀደምነት” እያጠሩ ከተቁጡ እንደመንጋም ቢንጋጉ ትግሉን ሊያራምዱ አይችሉም::

ከጥቂት ዓመታት በፊት “ታጠቅ” የጊዜውን ተግባራችንን ሲቀይስ “የማወቅ ዘመቻ” ብሎ ሰይሞት ነበር:: የዚያን ዘመን የኢት. ወጣቶች ለሬቮሉሽናዊ ቲዎሪ ገና ዓይናችንን የምንገል



ጥበት ወቅት ነበር:: ስለዚህም ይህ መሪ ቃል ጊዜውን የተከተለ ነበር:: አሁን በቂ አውቀናል “የማወቅ ዘመቻ”ይብቃው አንልም::በፍጹም:: ግን በረዥሙ የትግላችን ጉዳና ዛሬ ደግሞ አንዱ እርምጃ ወደፊት መርገጥ እንችላለን የሚል የጠበቀ ዕምነት አለኝ:: ዛሬ በአንድነታችን ከጠነከርን በትግላችን ሌላ የተቀናበረ ዘመቻ መክፈት እንችላለን:: ይኸውም “የመዋሀድ ዘመቻ” ነው::

“የማወቅ ዘመቻችን”ይህን ፍሬ የሰጠው ጭልጭልም ባሰው የአዱህሪወችና የወላዋዮች ርዕዮተዓለምና አስተሳሰብ ላይ ዱልን ስለተጎናጸፍን ነው:: “የመዋሀድ ዘመቻችን”ፍሬ እንዲሰጥ ደግሞ የማንኛውም ሬቮሉሽን ታሪክ ደጋግሞ እንዳሳየው ከአዱሃሪወችና ከወላዋዮች ሌላ በተራማጅነት ስም ከሚደባለቁት ቸኩለችና ተስፋ ቆራጮች፣ ከአጉል ተራማጆችና ከግራ ቀደሞች ጋርም የማያቋርጥ ትግል ይጠይቃል::

ጓዶች:: ነገሩ እኩ በጣም ቀላል ነው:: እስቲ ዛሬ ሁለት መቶ ሺህ ኢትዮጵያውያን በግፍ ያለቁበትን ርሀብና በሰፊው ህዝብና በኛ አስተሳሰብ መካከል ያለውን /ያስከተለውን/ ያስተሳሰብ ልዩነት እንመልከተው:: ተራማጅ ነኝ የሚል ሁሉ /ዳተኛውም ሆነ ቸኩሉ ሳይቀሩ/ የዚሁ እልቂት የመጀመሪያ ተጠያቂወች የሀይለሥላሴ መንግሥትና ደጋፊው ኢምፔርያሊዝም መሆናቸውን አበጥሮ ያውቃል:: የወሎና የትግራይ ህዝብ ግን የሞተው በድርቅ ምክንያት በገባው ክፉ ቀን አለቀ.ይላል:: የተረፈው ደግሞ “ፉሀፉሁ”ንጉሠ ነገሥቱ አስበው በላኩለት ዕርዳታ ተረፈ ይላል::እኛ የሞቱትን በስርዓቱ ከፋት ረገፉ እንላለን:: ህዝቡ ግን የተረፉት በሀይለሥላሴ በርታት ዳኑ ይላል::በነቃና ባልነቃ የፖለቲካ ህሊና መካከል ያለው ርቀት /ስለዚህም በኛ በተራማጆች ላይ የሚወድቀው ሀላፊነት ክብደት/ በነዚሁ ሁለት ዓለም ውስጥ በሚዋኙ የተለያዩ ግምቶች ሊለካ

ይቻላል:: ዛሬ የኢት. ተራማጆች ተግባር ሲቀየስ ከዚህ ተ
ጨባጭ ሁኔታ ሊነሳ ይገባዋል::

መንግሥቱ ለህዝቡ አያስብም:: በሌላ በተሻለ መንግ
ሥት መለወጥ አለበት:: ህዝቡ ተደራጅቶ ከታገለ ደግሞ በሌ
ሎች አገሮች እንደተደረገው ሁሉ ሊለወጥ ይችላል:: ይህ ሁሉ
ሉና ምን ያህል ግልጽና ቀላል አነጋገር ነው:: ግን መረዳት
ያቃተን ይህ ሁሉ በሚልዮን የሚቆጠረው ተበዝባዥ ህሊና ላይ
እንዲቀረጽ ከና ምን ያህል ትጋትና የተባበረ ጥረት እንደሚ
ጠይቅ ነው:: መረዳት የተሳነን ዛሬ ይህን ተቀዳሚና የግዱ
መደረግ ያለበትን ሬቮሉሽናዊ ተግባር በመናቅ የሆነ ያልሆነው
ን መውጫ 'ቲዎሪ'ስንፈልግ ምን ያህል የጨለማውን ዘመን እን
ደምናራዝመው ነው:: መገንዘብ ያልቻልነው ይህን ማህበራችን
ተቀዳሚነት ሊሰጠው የሚፈልገውን የመዋህዱ ዘመቻ ለማዱበሰበስ
'የቀኝ አዱር ባይ፣ ተቀልባሽ፣ የወንበር ሬቮሉሽናውያን ሴራ...
እያሉ ጊዜና አካባቢን የሳቱ 'ተራማጅ' ዐረፍተ ነገሮችን መወ
ርወር ወርቃዊ ጊዜን ማባከንና በኢት. ህዝብ ትግል፣ በኢት.
ህዝብ መከራ ከፉና ማሳገጥ መሆኑን ነው::

ታዲያስ 'የትግላችን ትርጉም' ምንድን ነው::በኔ አስ
ተያየት ሁለት ይዘቶች አሉት:: አንደኛ ትክክለኛውን መስመር
ባይታክቱ ማሳየት:: ሁለተኛ አባባችን ገደል ባይሰለቹ ማጋ
ለጥ::

መጀመሪያ ነገር የጊዜውን ተግባር አጥርተን የተረዳ
ን ተራማጆች በሙሉ ኃይላችንን አጣምረን በትጋት፣ በትዕግሥት፣
'አለሁ አለሁ አትርሱኝ' የማይለውንና የማይበለጨለጨውን፣ ህ
ዝቡን የማንቃትንና የማደራጀትን ተግባር ከስራ ላይ ማዋል አ
ለብን:: በተጨማሪም የቲዎሪ ዕውቀታችንን ለማዳበርም ተግተን
መሥራት አለብን:: በዚህ ትግል ሊረዳዳ የሚችለውን ኃይል
ሁሉ ለመሰብሰብ መንገዳችንን ግልጥልጥ አርገን ማሳየት አለ



ብን:: ወጣቱ ትውልዱ በታላቅ ጉጉት ለነጻነቱ ትግል ተነ
ሳስቷል:: ስንፈን ተግባራችንን ማየትና ለሰው ማሳየት ካቃ
ተን መንገዱን ለዳተኞችና ለተስፋ ቆራጮች፣ በተለይ ደግሞ
ለቸኩሎችና ለግራ ቀደሞች ክፍት መተው ይሆናል:: ሌኒን እን
ዳለው 'የግራ ቀደሞች ማየል ዕውነተኛ ሬቮሉሽናዊያን ሲሰንፉ
የሚመጣባቸው መቅጫ ነው::' በትጋትና በምንም በማይወናበዱ
ዕምነት ከሰራን ከዚህ ታሪክ ከሚያወርዱብን መቅጫ እንድናለን::

ግን የኛን መንገዱ ማሳየት ብቻ አይበቃም::'የትግላ
ችን ትርጉም' ሌላ ሁለተኛ ይዘት አለው ብለናል:: አባባችን
ገደልም እያጋለጡ ለትግል የጓጓው ትውልዱ እንዳይመረዝ ይህን
አዝማሚያ ከተራማጆች መነጠልና ማዳከም ያስፈልጋል:: ይህን
ንስ የምናደርገው ለምንድን ነው::

በኔ አስተያየት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ::
መጀመሪያ ነገር ይህ አዝማሚያ በተለይ 'መሣሪያ አንጨብጥ'
በሚለው ችኩል መልኩ ከሥራ ላይ ከዋለ በዛሬው ወቅት ለሬቮ
ሉሽናችን ፈጽሞ ሊለካ የማይችል ጥፋት ሊያደርስ ይችላል::
የስንት ዓመት ጥረትና ታሪክና ትግል ያፈራቸው ተራማጆች ጠላት
ጋር አለጊዜው ተጋፍጠው ቢረጀ ትግሉ የሚያስፈልጉትን ግንባር
ቀደሞችና አቀናባሪወች ያሳጡታል:: ሁለተኛ ደግሞ ገና በፖ
ለቲካ ዱርጅትና ትግል ልምዱ ያልዳበረን ህዝብ 'ተነስ' ብሎ
ማስጨፍጨፍ ዛሬ በከንቱ ማሳረዱ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ዘመናትም
በተስፋመቁረጥ ባህር ውስጥ ጨምሮ የገዥወችን ቀንበር እንደ
ቀበል መጋበዝ ይሆናል:: በአሜሪካ የኢት.ተማሪወች ማህበር
አንዳንዱ ጓዶች: 'ዛሬ የጦር ትግሉን አለመጀመር እንደ ክህ
ደት ይቆጠራል' ብለው ጽፈው የኢትዮጵያን ተራማጆች ወደ ጦሩ
ትግል ጋበዘዋቸዋል:: እኛ ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን ችኩልነት
በኢት. ሬቮሉሽን ላይ እንደተፈጸመ ወንጀል አዱርገን እንቆ
ጥረዋለን::

ግን ደግሞ ቸኩል ግራ ቀደሞቸን መዋጋት፣ ማጋለጥና ከወጣቱ ትውልድ መነጠል ያለብን ለዚህ ዓላማቸው ተባባሪ ለማ ሳጣት ብቻ አይደለም:: የነሱን ማወናበድ አስወግደን፣ የቲዎሪ ያቸውን ፋርሽነት አሳይተን ለጊዜው ዋና ተግባር የሚሰለፈውን ኃይል ለማዳበርና ሬቮልሽኑን ወደፊት ለማፋጠን እንድንችልም ነው:: ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት የቸኩሎች ማወናበጃ ባያጠቃው ኖሮ በሰሜን አሜሪካ የኢት. ተ. ማኅ ያለው ለጋ ጉልበት ለጊ ዜው ዋና ተግባር ቢውል የተጣመረ ኃይላቸን ሌላው ቀርቶ ስንት ስንት መጽሄቶች ሊያስወጣን ይችል ነበር:: ስንት መጽሄት ወደ ሀገር ያስገባልን ነበር:: ስንት ፖምፍሌት ወደ ሀገር መበተን ይቻል ነበር::ስንት የፕሮፖጋንዳ ጽሁፎች እየተረጎምን ማሳ ተም እንችል ነበር:: የጊዜውን ተግባራችንን በመተባበርና በቅ ልጥፍና በመሥራት ሬቮልሽኑን ስንት እናፋጥነው ነበር:: ለዚ ህም ነው አጉል ተራማጆችን መዋጋት አለብን የምንለው::

የኢትዮጵያ ተራማጆች የጊዜውን ዋና ተግባር አጥርተው አውቀው ለሌሎች ማሳየትና በትጋትም መታገል አለባቸው:: ይህ ተግባራችን በወጉ እንዲሰራ ደግሞ ታሪክ ጥሎብናል የምንለው አደራ፣ በኢት. ህዝብ ፊት አለብን የምንለው ተጠያቂነትም ይህን ብቅ ብቅ ማለት የጀመረ አዝማሚያም ታግለን እንድንጥ ለው ይጠራናል:: እርግጥ ይኸ ለጊዜው እስከዚህም እንደ ዋና ተግባር ሆኖ ላይቀርብ ይችላል:: ነገር ግን ዘላቂው ትግላ ቸን ይህንንም ሬቮልሽናዊ ተግባር መጨመሩ መረሳት የለበትም::

ንጋት ዓምደ

ይዘት


1. ርዕሰ አንቀጽ ገጽ 1

2. ረሃብ በኢትዮጵያ 5

3. የዓለም ጋዜጦች የኢትዮጵያን መንግሥት ያወግዛሉ 13

4. የሰብአዊ መብት ድምፅ 15

5. ለዲሞክራሲና ለፍትህ ለሚታገሉ የተደረገ ጥሪ 18

6. የጊኒ ቢሳዎ ህዝባዊ ትግል 20

7. የመንግሥቱን ጋዜጦች ስናገላብጥ 31
‹ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ ፍርጃ›

8፡ የትግላችን፡ ትርጉም ‹የመቀሃዱ ዘመቻ› 46

9. ይድረስ ለትግላችን 56

10. ኢትዮጵያ በዓለም ጋዜጦች 58
‹የኢትዮጵያ መንግሥት ለፖርቱጋል ይሰልላል›

ግጥ፡ ‹መንገደኛ› 62